GIJTR
Global Initiative for Justice
Truth & Reconciliation

# ራስን መገምገሚያ መሳርያ ስብስብ፡-

## ከግጭት ጋር በተያያዙ ከወሲባዊ ጥቃቶች ለተረፉ ሁለንተናዊ ድጋፍ ለማድረግ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችን እንዲሁም መልካም እድሎችን መተንተን

**የማእቀፍ ሰነድ**

### 1. አጠቃላይ እይታ

> **ይህ ሰነድ ከዓለም አቀ ኢኒሼቲቭ ለፍትህ፣ እውነት እና እርቅ (GIJTR's) ከግጭት ጋር የተያያዘ የወሲብ ጥቃት ራ**ስን-መገምገሚያ መሳሪያ ስብስብ ጋር አብሮ ይ **መጣል።**

እራስ-የመገምገሚያ መሳርያ ስብስብ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የሰርቫይቨሮች ኔቶርኮች ከእውነት፣ ፍትህ እና ፈውስ ጋር በተገናኘ የተራፊዎች ሁለንተናዊ ፍላጎቶች በእውዳቸው ውስጥ እንዴት በብቃት እንደሚሟሉ ለመተንተን እና ይህንን ትንታኔ ተጠቅመው ስልቶቻቸውን፣ ተግባራቶቻቸውን እና የወደፊት መርሃግብሮቻቸውን ለማሳወቅ ይጠቅማሉ። ከእውነት፣ ፍትህ እና ፈውስ ጋር በተያያዘ ተራፊዎች የተለያዩ እና የተሳሰሩ ፍላጎቶች እና ቅድሚያ የሚሰጧቸው ነገሮች እንዳሏቸው በመገንዘብ የግምገማው መሳሪያ ጥቅል ለድርጅቶች የተራፊዎች አስቸክዋይ እና የረዥም ጊዜ ፍላጎቶች፣ እና እነዚ ፍላጎቶች እንደት በጊዜ ሂደት ሊለዋወጡ እንደሚችሉ ለማገናዘብ ማእቀፍ ይሰጣል።

ባለፉት አስር ዓመታት ውስጥ ከግጭት የሚወጡ ማህበረሰቦችን በመደገፍ የGIJTR ልምድ ላይ በመመስረት፣ የመሳርያ ጥቅሉ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት (CRSV) ለደረሰባቸው ተራፊዎች የሚሰጠውን ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በሽግግር ፍትህ መነፅር የተራፊዎችን የእውነት፣ የፍትህ፣ የመካካሻ፣ የአለመደገም እና የመታሰቢያ/የማስታወሻ ፍላጎቶችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ያብራራል። የራስ መገምገሚያ መሣሪያ ጥቅሉን የሚጠቀሙ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የሰርቫይቨር ኔትወርኮች ስለሽግግር ፍትህ ሂደቶች እና ቃላት ፍቺዎች ያላቸው እውቀት ሊለያይ እንደሚችል በመገንዘብ የዚህ ሰነድ አላማ ከGIJTR እይታ እና ልምድ አንፃር የሽግግር ፍትህ ጽንሰ-ሀሳቦችን ማሰስ እና የራስ መገምገሚያ መሳርያ ጥቅሉ ውስጥ ለሚገኙ ቁልፍ ቃላት እና ሃሳቦች ትርጓሜዎችን መስጠት ነው። መደበኛ የሽግግር ፍትህ ስልቶች በፖለቲካዊ ፍላጎት ላይ ጥገኛ በመሆናቸው እነዚህን ስልቶች ለመመስረት አብዛኛውን ጊዜ ብዙ አስርተ አመታትን ስለሚወስድ በሰፊ የተለያዩ አውዶች ውስጥ ካሉ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ የሽግግር ፍትህ ውጥኖች ምሳሌዎች ተካተዋል።

## 2. ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሰርቫይቨሮች ለመደገፍ የGIJTR አቀራረብ መግቢያ

ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ማለት ሥርዓተ-ጾታን መሰረት ያደረገ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከግጭት ተነስቶ በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ በጾታ ይም በሥርዓተ-ጾታ ምክንያት የሚፈጸም ጥቃት ነው። በተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተመድ) “አስገድዶ መድፈር፣ የወሲብ ባርነት፣ የግዳጅ ዝሙት አዳሪነት፣ የግዳጅ እርግዝና፣ የግዳጅ ፅንስ ማስወረድ፣ አስገዳጅ ወሊድ መከላከል፣ የግዳጅ ጋብቻ እና ሌሎች ተመሳሳይ ክብደት ያላቸው በሴቶች፣ በወንዶች፣ በሴት ልጆች ወይም በወንዶች ልጆች ላይ የሚፈጸም ወሲባዊ ጥቃት አይነት”[1] ብሎ የሚተረጉመውን ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት በግጭት እና በሰብአዊነት ቀውሶች የተጎዱ አካባቢዎች ላይ ሰፊ ነው።

ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት አከናዋኞች እና ቅርጾች በተጎዱ አካባቢዎች ይለያያሉ፡- በአንዳንድ ዐውዶች ግጭት ውስጥ ያሉ ወገኖች ስልታዊ፣ ወታደራዊ ወይም ድርጅታዊ አላማዎችን ለማሳካት ይጠቀሙታል፤ በሌሎች አውዶች የህግ የበላይነት እና የጥበቃ ስርዓት መፈራረስ ወንጀለኞች (ግጭት ውስጥ ላልተሳተፉም ወገኖች ጭምር) በቀላሉ ምቹ የሆነ የመብት ጥሰት የሚፈጽሙበት ሁኔታን ይፈጥራል።

ሴቶች እና ሴቶች ልጆች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ባልተመጣጠነ ሁኔታ በሥርዓተ-ጾታ ልዩነት ላይ በተመሰረተ የጥቃት አይነት በሆነው ይጎዳሉ፤ በ2022 የተባበሩት መንግስታት ድርጅት (ተ.መ.ድ) ዋና ፀሃፊ በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ባወጣው ዓመታዊ ሪፖርት በሴቶች እና በልጃገረዶች ላይ የተዘገቡት ጉዳዮች ከ94% በላይ ናቸው። ከግጭት ጋር የተያያዘ የወሲባዊ ጥቃት ስርጭት በወንዶች ላይ የሚያሳዩ ጥናቶች እጅግ በጣም የተወሰኑ ናቸው፤ ነገር ግን ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ክስተቱ የተስፋፋ ነው። ለምሳሌ በ2008 በላይቤሪያ ውስጥ የተካሄደው ዘርፈ ብዙ፣ ህዝብን መሰረት ያደረገ፣ በዘፈቀደ ክላስተር የተሰራ ጥናት እንዳመለከተው 32.6% ወንድ የቀድሞ ተዋጊዎች ወሲባዊ ጥቃት ደርሶባቸዋል። በግምት አንድ ሦስተኛ የሚሆኑት የአዋቂ ወንድ የቀድሞ ተዋጊዎች ወሲባዊ ጥቃት ያጋጠማቸው ሲሆን በአንፃሩ ወደ 7% ብቻ የሚሆኑት በውጊያ ውስጥ ያልተሳተፉ ወንዶች ወሲባዊ ጥቃት አጋጥሟቸዋል፤ በላይቤሪያውያን ወንዶች (ተዋጊዎች እና ተዋጊ ያልሆኑ) ላይ ለተፈጸመው ለአብዛኛዎቹ ወሲባዊ ጥቃቶች ወታደሮች ወይም አማፂዎች ተጠያቂ እንደሆኑ ተዘግቧል።[2] በሲሪላንካ ውስጥ በነበረው የጎሳ የእርስ በርስ ጦርነት ወቅት በግምት ከ9-21% የሚሆኑ ወንዶች የሆነ አይነት ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት እንዳጋጠማቸው ጥናቶች ያሳያሉ።[3]

ለሁሉም ሥርዓተ-ጾታ ግለሰቦች የማሳወቅ እንቅፋቶች –– መገለልን፣ ደህንነቱ ያልተጠበቀ የማሳወቅያ ዘዴዎች፣ በተቋማት ውስጥ ወደ ወሲባዊ ጥቃት መፈቀድ ወይም መታገስ የሚያመሩ ጎጂ ማኅበራዊ ደንቦች፣ የአካላዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት ችግሮች እና ከወንጀለኞች፣ ከቤተሰብ ወይም ከማህበረሰብ የሚመጡ የበቀል ፍርሃትን ጨምሮ –– በመደበኛ መንገዶች የማሳወቅ ማነስን ውይም እጥረትን ያስከትላል።

**The Global Initiative for Justice, Truth and Reconciliation**

In 2014, the International Coalition of Sites of Conscience (ICSC) launched the Global Initiative for Justice, Truth and Reconciliation (GIJTR), a consortium of nine international organizations focused on offering holistic, integrative and multidisciplinary approaches to issues of truth, justice and reconciliation. GIJTR works primarily with local populations, civil society organizations, survivors and governments to develop transitional justice approaches that are victim-centered, collaborative, and support dignity, respect, inclusion, and transparency in societies emerging from conflict or periods of authoritarian rule. Since its founding, GIJTR has engaged 801 local civil society organizations; 78 countries; 43 publications; collection of over 8,000 narratives of human rights violations; and supported 588 civil society organizations dealing with human rights violations.

**For more information, please visit gijtr.org.**

GIJTR
Global Initiative for Justice
Truth & Reconciliation

በተጨማሪም ወንዶች፣ ወንድ ልጆች እና የተለያየ ጾታዊ ዝንባሌ ያላቸው ሰዎች፣ የሥርዓተ-ጾታ ማንነት፣ የሥርዓተ-ጾታ አገላለጽ እና የጾታ ባህሪያት (SOGIESC) ያላቸው ሰዎች እንዳያሳውቁ የሚከለክሉ ልዩ ተግዳሮቶች አሉ፤ እነዚህም እንደ ተጠቂዎች እንዳይቆጠሩ እና/ወይም የወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎችን በማሳወቅ ምክንያት ወንጀለኛ ማድረግ የሚችሉ የህግ ማዕቀፎችን ያካትታል። ስለዚህ የስርጭት አሃዞች እንደ ግምቶች መወሰድ አለባቸው እንዲሁም ትክክለኛው ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ተጠቂዎች ቁጥር በጣም ከፍ ያለ ይመስላል።

ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት በደረሰባቸው ግለሰቦች እና በማህበረሰባቸው ላይ ያለው ዘላቂ ተጽእኖ ዘርፈ ብዙ እና ሁለገብ ምላሽን ይጠይቃል፤ ይህም የስነ-ልቦና፣ የህክምና፣ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እና የህግ ድጋፍን ያካትታል። የሰብአዊ መብቶች ህግ እንደሚያሳውቀው ከባድ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት የሚደርስባቸው ሰዎች ስነ-ልቦናዊ ህክምናን እና ሌሎች ማቃለያ እርምጃዎችን የማግኘት መብት አላቸው[4] እንዲሁም መንግሥታት የሰርቫይቨሮች አስቸኳይ እና የረዥም ጊዜ ፍላጎቶችን የማሟላት ሃላፊነት አለባቸው። ሆኖም ግን፣ እውነታው ዛሬ በዓለም ዙሪያ ያሉ ብዙ ሰርቫይቨሮች ወደ ማኅበረሰባቸው ለመቀላቀል እና ሕይወታቸውን መልሰው ለመገንባት የሚያስፈልጋቸውን ዘላቂ እርዳታ ይቅርና መሠረታዊ እንክብካቤ እንኳ ለማግኘት ይቸገራሉ።

ሰርቫይቨሮች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት አጠቃላይ የምላሽ አካል ሆነው ፍትህን መፈለግ መቻል አለባቸው። ሰርቫይቨሮች ፍትህን ለመተርጎም እንዴት እንደሚመርጡ ከሀገር ሀገር፣ ከክፍለ ሀገር ክፍለ ሀገር እና ከሰርቫይቨር ሰርቫይቨር ይለያል። ለአንዳንዶች ስለ ስቃያቸው ይፋዊ እና ህዝባዊ እውቅና መጠየቅን ወይም ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ እና ወደ ማህበረሰባቸው እንዲቀላቀሉ ላይ ትኩረት ማድረግን ያካትታል። ለሌሎች ደግሞ የገንዘብ ማካካሻ አቅርቦት ላይ ወይም ጥቃት የፈፀሙባቸውን በህግ ተጠያቂነት በማድረግ ሊገኝ ይችላል።

ከቅርብ አሥርተ ዓመታት ወዲህ በዓለም አቀፍ፣ በቅይጥ እና በሀገር ውስጥ ፍርድ ቤቶች እና ጊዜያዊ ፍርድ ቤቶች (tribunals) ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀል ፈፃሚዎች ላይ በመፍረድ ረገድ ከፍተኛ መሻሻል ታይቷል። ነገር ግን ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ተጠያቂነት ማግኘት አሁንም በጣም አስቸጋሪ ነው፤ ብዙ ሰርቫይቨሮች ባልተገባ እፍረት፣ በመገለል እና ወንጀለኞቻቸው በስልጣን ላይ እስከቆዩ ድረስ ያለመቀጣታቸው ፍርሀት ምክንያቶች ያሳለፉትን አፍኖ ለመያዝ ተገድደዋል። በህግ የመቀጣት መጠን የለም ለማለት የሚቃረብ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሰርቫይቨሮች እነሱን ያማከሉ ፕሮቶኮሎች ባለመኖራቸው እና ለፍላጎታቸው ቅድሚያ የማይሰጡ የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቶች በመኖራቸው ምክንያት ተጠያቂነትን በመፈለግ ሂደት በተደጋጋሚ ይጎዳሉ እና ድጋሚ የስሜት ቀውስ ይደርስባቸዋል። [5]

የGIJTR ስራ የተመሰረተው ከሁከትና ብጥብጥ ባለፈባቸው ሀገራት ውስጥ ሁሉም የህብረተሰብ አባላት—በተለይ እንደ ሴቶች፣ አናሳ እና የግጭት ሰርቫይቨሮች የመሳሰሉ የተገለሉ ቡድኖች—አገራቸውን መልሶ ለመገንባት ዋና ሚና መጫወት ካልቻሉ ዘላቂ ሰላም ሊመጣ አይችልም በሚለው እምነት ላይ ነው። አንዳንድ የሽግግር የፍትህ ሂደቶች እነዚያን ቁልፍ ድምጾች በንቃት ማሳተፍ ተስኗቸው ይልቁንም በስልጣን ላይ ያሉን ሰዎች ልምድ እና አስተያየት ቅድምያ የሚሰጡ ከላይ ወደ ታች የሆኑ ሂደቶችን መርጠዋል፤ የGIJTR ስራ በግጭት በቀጥታ የተጎዱ ማህበረሰቦች ውስጥ ባሉ የሰርቫይቨሮችን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን እውቀት እና ልምድ ያማከለ ሆኖ ለእነርሱም እውነትን፣ ፍትህን እና ማካካሻን በተለያዩ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ መንገዶች እንዲከታተሉ ስልጠና እና መሳሪያዎች መስጠት ነው።

ከዚህ ዳራ አንጻር GIJTR በመላ መርሃ ግብሮቹ ውስጥ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሰርቫይቨሮች ድጋፍ ቅድሚያ ሰጥቷል። በመካከለኛው ምስራቅ የዳኢሽ ግፍን ያሳለፉ ሰርቫይቨሮች ጋር ከመስራት ጀምሮ ለምሳሌ ከግጭት ጋር በተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት የተወለዱ ህጻናት ልዩ የሆነ የመልሶ ማቋቋም ፍላጎቶችን ርዕስ የሚሸፍን ለሰብአዊ መብቶች ባለሙያዎች የአሰልጣኞች ስልጠና መሳሪያ ጥቅሎች በማዘጋጀት GIJTR ለሰርቫይቨሮች አስቸኳይ እና የረጅም ጊዜ ፍላጎቶች በተለያዩ የሽግግር የፍትህ ውጥኖች አማካይነት ምላሽ ሰጥቷል።

ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ የሮሂንጊያ ማህበረሰብ አባላት ከምያንማር ጦር ኃይል የሚደርስባቸውን ስቃይ ሸሽተው በስደት በሚኖሩባት **ባንግላዴሽ** ውስጥ የGIJTR አጋሮች በማህበረሰብ ለሚመሩ የስነዳ ተልእኮዎች ላይ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እንዲሰንዱ የሴት መሪዎችን ለይተው አሰልጥነዋል። ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስትን ተከትሎ ወሲባዊ ጥቃትን በተመለከተ ያለው መረጃ ውስን ቢሆንም በ2018 ለተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት ባቀረበው ሪፖርት በ 2016 እና 2017 በጦር ኃይሉ "የማጽዳት ዘመቻ" ወቅት በራኪን ክልል ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ የሮሂንጊያ ሴቶች እና ልጃገረዶች እንደተደፈሩ፣ በቡድን እንደተደፈሩ እና/ወይም ሌሎች ወሲባዊ ጥቃቶች እንደተፈፀመባቸው ገለልተኛ አለም አቀፍ የምያንማር እውነታን ፍለጋ ተልዕኮ ሰንዷል። በአሁኑ ጊዜ ባንግላዴሽ ውስጥ የሚኖሩት አብዛኞቹ የሮሂንጊያ ስደተኞች ሴቶች እና ህጻናት ሲሆኑ ከ40% በላይ የሚሆኑት እድሜያቸው ከ12 አመት በታች ነው። ሌሎች ዓለም አቀፍ ኤጀንሲዎች ከሮሂንጊያ ማህበረሰብ ጋር የስነዳ ውጥኖችን ሲያካሂዱ በአጠቃላይ እንደ አስተርጓሚዎች ወይም "አስተካካዮች" ብቻ ከሚሰሩ የሀገር ውስጥ አክቲቪስቶች ጋር ነው። የGIJTR ልምድ ግን ከማህበረሰቡ ውስጥ የተወጣጡ የስነዳ ባለሙያዎች እነዚህን ጥረቶች እንዲመሩ ማሰልጠን እጅግ የበለጠ ውጤታማ አካሄድ መሆኑን አሳይቷል። ከዓለም አቀፍ ጥረቶች በተቃራኒ መልኩ በሀገር ውስጥ የሚመሩ እና የተቀናጁ የሲቪል ማህበረሰብ የስነዳ መርሃ-ግብሮች በሰርቫይቨሮች መካከል መተማመንን ይፈጥራሉ፣ በውጫዊ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከሚመሩት ጥረቶች ወሰን ውጭ ላሉ ማህበረሰቦች ይደርሳሉ እና ለወደፊት የሽግግር የፍትህ ሂደቶች መሰረት ይጥላሉ። ስለወሲባዊ ጥቃት መወያየት በማህበረሰቡ እንደ ነውር ስለሚቆጠሩ ሴቶች እና ልጃገረዶች የመብት ጥሰት ልምዳቸውን ለሴት አስተባባሪዎች የማካፈል እድላቸው ብዙ ጊዜ ከፍተኛ በመሆኑ ሴት መሪዎችን በስነዳ ማሰልጠን ታሪካቸውን ለመሰብሰብ እና ለማቆየት አስፈላጊ ነበር።

**በዩክሬን**—ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ማስረጃዎችን የመሰብሰብ እና የማቀናበር ትንሽ የቀድሞ ልምድ ያላቸው ድርጅቶች አሁን ይህንን ስራ የአለም አቀፍ ደረጃዎችን ይዘው እንዲሰሩ ከፍተኛ ጫና እየደረሰባቸው ሲሆን በየካቲት 2022 ዓ.ም የሩሲያን ሙሉ ወረራ ተከትሎ የGIJTR አጋሮች ተመሳሳይ ዘዴ በመጠቀም ለሲቪል ማህበረሰብ የስነዳ ባለሙያዎች ስልጠና እና የስነ-ልቦና ድጋፍ ሰጥተዋል። ብዙ ሰርቫይቨሮች በመገለል ምክንያት ለመናገር በሚፈሩበት አውድ ውስጥ በጊዜ ሂደት ቀስ በቀስ የምስክሮች እና የሰርቫይቨሮች አመኔታን ለመገንባት ወደ ተመሳሳይ ሰፈራዎች ደጋግመው መሄድ የቻሉት የዩክሬን ድርጅቶች ስራ እነዚህን ወንጀሎች ለማጋለጥ፣ ሰርቫይቨሮችን ወደ የድጋፍ አገልግሎቶች ለመጥቀስ እና ለተጠያቂነት ጥረቶች አስተዋፅኦ ለማድረግ ወሳኝ ነው።

**በጋምቢያ** በ2018 ዓ.ም የሀገሪቱ እውነት፣ ዕርቅ እና ማካካሻዎች ኮሚሽን ከመጀመሩ በፊት በነበረው የሀገሩ ምክክር ወቅት ሴቶች ግብአት ከመስጠት ተገልለው ነበር። ኮሚሽኑ ሥራ ከጀመረ በኋላ ሴቶች በተጠያቂነት ሂደት ውስጥ በደህንነት እንዲሳተፉ ለማስቻል በደል ለደረሰባቸው ወይም የስሜት ቀውስ ለደረሰባቸው ሴቶች ስማቸው እንዳይገለጽ እና ግላዊነታቸው እንደሚያስፈልግ የሚያሳዩ በርካታ ማስረጃዎች ቢኖሩም ኮሚሽኑ ሴቶች የምስክርነት ቃል የሚሰጡበት ደህንነታቸው የተጠበቁ ቦታዎችን ማቅረብ አልቻለም። የGIJTR ልምድ ሴቶችን ጨምሮ የተገለሉ ቡድኖችን በሽግግር የፍትህ ሂደቶች ውስጥ ማሳተፍ እንደሚያስፈልግ ያሳያል፤ ምክንያቱም እነዚህን ሂደቶች የማዳበር አካል ካልሆኑ ወደ ፊት ለማራመድ ጥሩ አቋምም ሆነ ጥልቅ ፍላጎት የላቸውም። በጋምቢያ ውስጥ ለዚህ አንገብጋቢ ፍላጎት ምላሽ ለመስጠጥ GIJTR ከሀገር ውስጥ አጋር ሴቶች በነጻነት እና አመራር ጋር በሦስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ለሴቶች ብቻ "የማዳመጥ ክበቦችን" ለማካሄድ ሠርቶ ግኝቶቹን እና ምክረ-ሃሳቦቹን በሪፖርት አጠናቅሯል። የጋምቢያ የፍትህ ሚኒስቴር በአዎንታዊ መልኩ የተቀበለው ይህ ሪፖርት የእውነት፣ ዕርቅ እና ማካካሻዎች ኮሚሽን ለጋምቢያ ሴቶች እና ልጃገረዶች ፍትህ እንዲሰጥ በጋምቢያ ማህበረሰብ ውስጥ ከአምባገነኑ ስርዓት በፊት የነበሩት እና ዛሬም የቀጠሉት የወሲባዊ እና ሥርዓተ-ጾታን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችን መንስኤዎቻችውን ማወቅ እና መፍትሄ መስጠት አለበት ሲል ደምድሟል።

በ2016 የGIJTR አጋሮች የሽግግር ፍትህ ፅንሰ ሀሳቦች ግንዛቤን ለማሳደግ እና የሽግግር ፍትህ መርሃ-ግብሮች ለሰርቫይቨሮች ፍላጎት ምላሽ ሰጪ መሆናቸውን እንድያረጋግጡ ሰርቫይቨሮች፣ አክቲቪስቶች፣ እና ምሁራን የሽግግር ፍትህ መርሃ ግብሮችን በአካባቢያቸው ማህበረሰቦች ውስጥ ለመንደፍ እና ለመተግበር የምያስፈልጋችውን ችሎታ እና ገንዘብ ለመስጠት **የመካከለኛው ምስራቅ እና ሰሜን አፍሪካ (MENA) የሽግግር ፍትህ አካዳሚን** አቋቁመዋል። በአካዳሚው በኩል GIJTR በMENA አካባቢ ውስጥ ከሰብአዊ መብት ጥሰት ሰርቫይቨሮች ጋር ለሚሰሩ ልዩ ልዩ ባለሙያዎች የቴክኒክ እና የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል፤ ስለ ተለያዩ የሰነድ አይነቶች ያላቸውን ግንዛቤ ለመጨመር፣ ያቀረቡት ማስረጃ ለፍትህ እና ለፈውስ ዓላማዎች እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል፣ እና ከእነዚህ ሂደቶች ጋር በሚገናኙበት ጊዜ መብቶቻቸውን ለማሳደግ ከሶሪያውያን ሴቶች ጋር ቀደም ሲል ታስረው ከነበሩት የሶሪያ ጋር አውደ ጥናቶችን ያደረገ አንድ የአካባቢው አጋር ጨምሮ። ከተሳታፊዎች የተሰጡ አስተያየቶች ስለአውደ ጥናቱ አስፈላጊነት ሲናገሩ በተሳተፉት ሴቶች መካከል የላቀ የኃላፊነት ስሜት እንዲፈጠር አድርጓል ብለዋል።

በ2009 **በጊኒ** ስታዲየም እልቂት ቢያንስ 150 ሰላማዊ ሰዎች ተገድለው እና በደርዘን የሚቆጠሩ ሴቶች እና ልጃገረዶች ወሲባዊ ጥቃት ደርሶባቸው ካለፈ በኋላ GIJTR ከጊኒ አጋር መስከረም 28 ቀን እልቂት የተጎጂዎች፣ ወላጆች እና ወዳጆች ማኅበር (AVIPA) ጋር አንድ ላይ ለስድስት ዓመታት በሚቆይ ጊዜ ውስጥ ከሽግግር ፍትህ ጋር በተያያዙ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አቅማቸውን ለማጎልበት የሰራ ሲሆን ስራውም አሳታፊ እውነትን ይፋ ማድረግ፣ የአዕምሮ ጤና እና የስነ-ልቦና ድጋፍ፣ መታሰቢያነት፣ የሥርዓተ-ጾታ ፍትህ እና ጭካኔ የተሞላባቸውን ድርጊቶች መከላከልን ያካትታል። AVIPA ከGIJTR ድጋፍ ጋር በበኩሉ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮችን የስነ-ልቦና ድጋፍ ቡድኖችን አቋቁሟል፣ በኪነጥበብ ላይ በተመሰረቱ "የሰውነት ልየታ" አውደ ጥናቶች እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ላይ አሳትፎዋቸዋል፣ ከጎናቸው በመሆን በቅርቡ የተጀመረው የስታዲየም እልቂት ሙከራ እንዲጀመር አጥብቆ ደግፏል እና ሴቶች እና ልጃገረዶች የተከሰቱ ያሉ ወሲባዊ እና በሥርዓተ-ጾታ ላይ የተመሰረቱ ጥቃቶችን ሪፖርት እንዲያደርጉ እና ለሳይኮማህበራዊ፣ ለህክምና እና ለህግ ድጋፍ አገልግሎቶች ሪፈራሎችን እንዲቀበሉ የሚያስችል የስልክ መስመር አቋቁሟል።

በመጨረሻም ከእነዚህ እና ከሌሎች አውዶች GIJTR የተማረውን ትምህርቶች ለማካፈል ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮችን በመደበኛ እና ኢ-መደበኛ የሽግግር ፍትህ ዘዴዎች ለመደገፍ ሁለንተናዊና ሰርቫይቨሮችን ያማከሉ አቀራረቦችን የሚገልጹ በርካታ **መሳሪያ ጥቅሎችን እና ግብአቶችን** ፈጥሯል። እነዚህም "እውነት፣ ዳቦ እና ሻይ:- ከግጭት ጋር የተያያዘ የወሲባዊ ጥቃት ሴቶች ሰርቫይቨሮችን እና በጦርነት የተወለዱ ህጻናትን መልሶ ለማዋሃድ የሚያስችል መሳሪያ ጥቅል" ተብሎ የተሰየመውን የሰርቫይቨሮች ታሪኮችን ግንዛቤ በማሳደግ እና በመብቶች ላይ የተመሰረቱ የጥብቅና ስልቶችን በመጋራት ላይ ያተኮረ የአካል ካርታ መሳሪያ ጥቅልን እና ሴቶችን በሽግግር የፍትህ ሂደቶች ውስጥ ትርጉም ባለው መልኩ ለማካተት በሴቶች ከሚመሩ መሰረታዊ ድርጅቶች የተሰጡ ምክሮችን የሚጋራ በሴቶች እና የሽግግር ፍትህ ላይ የተዘጋጀ መሳሪያ ጥቅልን ያካትታል።

> **ለምን የኛን ታሪክ እንደሚሰበስቡ አንድ ጊዜ እንኳን ሳይነግሩን ያንን መረጃ ሰብስበው ጥናት ያደረጉብን ድርጅቶችና ግለሰቦች ነበሩ።**

## 3. ቁልፍ ቃላት

**ተጎጂ፣ ሰርቫይቨር:-** ይህ የመሳሪያ ጥቅል ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ያጋጠማቸውን ግለሰቦች ለማመልከት ሁለቱንም "ተጎጂ" እና "ሰርቫይቨር" ቃላት የሚጠቀመው እነዚህ ቃላት ጥቅም ላይ የዋሉበት አውድ ሊለያይ እንደሚችል በመገንዘብ እና አንድ ግለሰብ "ተጎጂ" ወይም "ሰርቫይቨር" ተብሎ ለመታወቅ በዋናነት በምርጫቸው እና ራስን በመግለፅ ስለሚወሰን ነው። "ተጎጂ" ብዙውን ጊዜ የተጎጂነት ክስተት እና የህግ አውዱን በማጣቀስ እና ሁሉም ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸው ተጎጂዎች ከወንጀሉ በህይወት እንደማይተርፉ በጣም አሳዛኝ የሆነውን እውነታን ለማንፀባረቅ ይጠቅማል። "ሰርቫይቨር" ወሲባዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ግለሰቦች መቋቋምን እና አቅምን ያጎላል፣ በሥነ ልቦና እና በማህበራዊ ድጋፍ ዘርፎች በብዛት የተለመደ ነውእና ስለዚህም በዚህ መሳሪያ ጥቅል ውስጥ በብዛት ጥቅም ላይ ይውላል።

**ሰርቫይቨርን-ያማከለ አቀራረብ:-** ሰርቫይቨርን ያማከለ አቀራረብ ማለት ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ያጋጠመውን ሰው መብቶችን፣ ፍላጎቶችን፣ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮችን እና አቅሞችን ማወቅ እና ቅድሚያ መስጠት ማለት ነው። ይህ አቀራረብ ደጋፊ አካባቢን ይፈጥራል፣ ሰርቫይቨሩን ማገገም ለማበረታታት ደህንነትን እና ክብርን ያረጋግጣል እና ሊኖሩ ስለሚችሉ ጣልቃ ገብነቶች ውሳኔ የመስጠት አቅምን ያጠናክራል።

**በስሜታዊ ቀውስ-መረጃ የተደገፈ አቀራረብ፦** ስሜታዊ ቀውስ የሚመጣው አንድ ግለሰብ እንደ ጎጂ ወይም ለሕይወት አስጊ ናቸው ብሎ ባሳለፋቸው ክስተት፣ ተከታታይ ክስተቶች ወይም የሁኔታዎች ስብስብ ነው። ለግለሰቡ ልዩ ቢሆንም በአጠቃላይ ስሜታዊ ቀውስን ማሳለፍ ዘላቂ አሉታዊ ተፅእኖዎችን ሊያስከትል ይችላል፤ የመሥራት ችሎታን እና የአዕምሮ፣ የአካል፣ የማህበራዊ፣ የስሜታዊ፣ እና/ወይም የመንፈሳዊ ደህንነት መጠበቅን ይገድባል። በስሜታዊ ቀውስ መረጃ የተደገፈ አቀራረብ አላማው ስሜታዊ ቀውስ እንዴት ግለሰቦች እና ማህበረሰቦች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር እና የደህንነት ስሜት እንዲሰማቸው ወይም ከድጋፍ አገልግሎቶች እና ከሰራተኞቻቸው ጋር ታማኝ ግንኙነቶችን በማዳበር ላይ የባለሙያዎችን ግንዛቤ ለማሳደግ ነው።

**ሥርዓተ ጾታን-ያማከለ አቀራረብ፦** ሥርዓተ-ጾታን ያማከለ አቀራረብ የእያንዳንዱን ሰርቫይቨር ክብር እና የግል ማንነት ስሜት ማክበር፣ የሰርቫይቨር ልምዶች ላይ ሥርዓተ-ጾታ የሚያመጣውን ተፅእኖ መከታተል፣ በታሪክ ላልተካተቱ ሰርቫይቨሮች እና ወንጀሎች ቦታ መስጠት እና በጾታ ማንነታቸው የተነሳ የተለያዩ ግለሰቦች በግጭት እና በብጥብጥ የሚጎዱበትን በርካታ መንገዶችን ማወቅን ያካትታል።

**የሰርቫይቨር ኔትዎርኮች፦** እነዚህ ኔትዎርኮች ለመወያያ እና ለጋራ መረዳጃ ቦታ በመስጠት በሰርቫይቨሮች መካከል መተባበርን ለመፍጠር የተገነቡ ናቸው። የሰርቫይቨር ኔትዎርኮች ሰርቫይቨሮች የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ እንዲያገኙ፣ ስለተሞክሯቸው የጋራ ትውስታዎችን እንዲያካፍሉ እና የጥብቅና እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን በማካሄድ የጋራ ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ነገሮች ማሳደግ ይችላሉ።

**የሲቪል ማህበረሰ ድርጅቶች፦** የጋራ ጥቅም ባላቸው ሰዎች በመመራት እነዚህ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የበጎ ፈቃድ ዜጎች ቡድኖች በአካባቢ፣ በሀገር አቀፍ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተደራጅተው የተለያዩ አገልግሎቶችን እና የሰብአዊነት ተግባራትን ያከናውናሉ፤ የዜጎችን ስጋት ወደ መንግስታት ያመጣሉ፣ ፖሊሲዎችን ይከታተላሉ እና በማኅበረሰባቸው ውስጥ የፖለቲካ ተሳትፎን ያበረታታሉ።

**ፍትህ እና ተጠያቂነት፦** ይህ የሚመለከተው የተጠያቂነት መንገዶችን፣ የመልሶ ማቋቋምን እና ወንጀል የተፈፀመባቸውን ተጎጂዎች የሰብአዊ መብቶች ሙሉ ተጠቃሚነትን ነው። ፍትህ የተለያዩ ቅርፆችን ሊይዝ እና በተለያዩ መሳሪያዎች ሊገኝ ይችላል፤ እነዚህም የሽግግር የፍትህ ስልቶችን፣ እንዲሁም እውነትን ይፋ ማድረግ፣ መታሰቢያን/ማስታወሻን፣ ማካካሻን፣ ውጤታማ መፍትሄዎችን፣ የወንጀሎች እና ጥሰቶች እውቅናን ወይም ግንዛቤን፣ መደበኛ የፍትሐ ብሔር ወይም የወንጀል ፍርድ ቤት ሂደቶች፣ እንዲሁም ኢ-መደበኛ እና ባህላዊ የፍትህ ዓይነቶችን ያካትታሉ።

**LGBTQI+፦** የሌዝቢያን፣ የጌይ፣ የሁለቱም ጾታ፣ ጾታ የቀየሩ፣ ኢንተርሴክስ እና ክዌር ምህጻረ ቃል፤ የመደመር ምልክቱ የተለያየ SOGIESC ያላቸውን ሌሎች ቃላት በመጠቀም የሚለዩ ሰዎችን ይወክላል።

## 4. የሽግግር ፍትህ ጽንሰ-ሐሳቦች መግቢያ

“የሽግግር ፍትህ” ማለት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በሰፋት የሚከሰት በደሎችን እና ጥሰቶችን ለመፍታት የታለሙ ስልቶችን እና ሂደቶችን ለማካተት የሚያገለግል ቃል ነው። እነዚህ አካሄዶች ከግጭት ወይም ከአምባገነን አገዛዝ ጊዜ ለወጡ ማህበረሰቦች የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ትሩፋት ለመፍታት ገንቢ ዘዴን ይሰጣሉ። በወሳኝ መልኩ የሽግግር ፍትህ ሰርቫይቨርን ያማከለ ሂደት ሆኖ ለግለሰቦችም ሆነ ለአጠቃላይ ህብረተሰቡ መፍትሄ እና እውቅና የሚሰጥ ሂደት መሆን አለበት። የመጨረሻ ግቡ ፍትሃዊ፣ የተከበረ እና የታረቀ ማህበረሰብ መመስረት ነው። በፍትህ እና በሰብአዊ መብቶች መርሆዎች ላይ የተመሰረተ ቢሆንም የሽግግር ፍትህ እንደ አሰራሩ በጊዜ ሂደት በአመፅ እና በጭቆና የተበላሹትን ሰፋ ያሉ ማህበራዊ ግንኙነቶችን በመጠገን ላይ በልዩ ሁኔታ ያተኩራል።

የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እና የጅምላ አሰቃቂ ወንጀሎችን ለመፍታት የሚረዱ የሽግግር ፍትህ ሂደቶች የረዥም ጊዜ፣ ፍትሃዊ እና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ልዩ እና የተወሰኑ የተቀናጁ ዘዴዎችን ይፈልጋሉ። እነዚህ ዘዴዎች በተደጋጋሚ ወደ አምስቱ የሽግግር ፍትሕ ምሰሶዎች የተከፋፈሉ ናቸው፦ እውነት፣ ፍትህ፣ ማካካሻዎች፣ የአለመደገም ዋስትና እና መታሰቢያ/ማስታወሻ። እነዚህ አምስቱ ምሰሶዎች እርስ በርስ የሚደጋገፉ ናቸው፤ ምክንያቱም እያንዳንዳቸው ለሌሎቹ ዕርቅን የሚደግፍ፣ የጥቃትን መደገም የሚከላከል እና ለሰርቫይቨሮች እና ለተጎጂዎች ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ ሁሉን አቀፍ ሂደትን ያቀርባሉ።

## ከዚህ በታች ከአምስቱ የሽግግር ፍትህ ምሰሶዎች ጋር በጣም የሚዛመዱ የተለመዱ የድጋፍ ዘዴዎች ይገኛሉ፦

**እውነት፤** የተፈጸሙ ጥሰቶችን እውቅና መስጠት እና መሰነድ በግለሰብ ደረጃ ለተጎጂዎች እና ለሰርቫይቨሮች እና ሰፋ ባለ ማህበራዊ ደረጃ የጥሰቶችን እምቢታ ወይም መደገምን ለማስወገድ አስፈላጊ ናቸው።

**እውነትን ይፋ የማድረግ ውጥኖች** ስለተፈጸሙት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ምንነት መረጃን ለማግኘት፣ የግጭት መሰረታዊ መንስኤዎችን ለመፍታት፣ ለሰርቫይቨሮች ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ቦታ ለመስጠት እና ሰፊ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ለማሸነፍ ምክሮችን ለመስጠት በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ እንዲሄዱ የተነደፉ ልዩ የእውነት ኮሚሽኖች ወይም ሀገር አቀፍ የእውነት ተናጋሪ መርሃ ግብሮች መፍጠርን በተደጋጋሚ ያካትታሉ።

**ፍትህ፤** ይህም ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና አለም አቀፍ ወንጀሎች የፈጸሙትን መለየትን እና ለፍርድ ማቅረብን ያካትታል። የበቀል አይነት ቢሆንም “ፍትህ” በዚህ መልኩ ተጎጂዎች እና ሰርቫይቨሮች ለደረሰባቸው ጥሰቶች ተጨማሪ እውቅና ይሰጣል እና ለተመሳሳይ ጥሰቶች መከላከያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።

እዚህ ላይ ዋናው ዘዴ **የወንጀል ክሶች** ሲሆን ይህም በከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት የተከሰሱትን በፍርድ ቤት መመርመርን እና መክሰስን ያካትታል። እነዚህም የሀገር ውስጥ እና የውጭ ተዋናዮች ተሳትፎን በሚያካትቱ በሀገር ውስጥ፣ በዓለም አቀፍ፣ በቅይጥ እና በድብልቅ ፍርድ ቤቶች ውስጥ ሊከናወኑ ይችላሉ።

**ማካካሻ፤** የማገገሚያ ቁልፍ ሂደት የሆነውን ማካካሻዎችን ለግለሰቦች እና ለቡድኖች የተወሰደባቸውን መመለስን፣ ገንዘብ መክፈልን እና ማገገሚያ መስጠትን ጨምሮ የተለያዩ የማረም መንገዶችን ሊወስድ ይችላል። በቁሳቁስ እና በምሳሌያዊ መልኩ ሊቀርቡ የሚቺሉት ማካካሻዎች ሁለቱም የጉዳት ስቃይ ለመከሰቱ እና ለማስተካከል ሙከራ ለመደረጉ ተጨባጭ እውቅና ሆነው ያገለግላሉ። በሰፊ ማህበራዊ ደረጃ ማካካሻዎች ለተጎጂዎች እና ለሰርቫይቨሮች ርህራሄን ሊገነቡ ይችላሉ።

የሰብአዊ መብት ጥሰት ለደረሰባቸው ተጎጂዎች በስቃይ ካሳለፉት ጥቃት ወይም ጥፋት የሚመጡን የረዥም ጊዜ መዘዞችን ለመፍታት ማካካሻዎች በፍትህ እና በአስተዳደር ባለስልጣናት ስር ተዳድረው ሁለቱንም ቁሳዊም ሆነ ተምሳሌታዊ የጥቅም መርሃ ግብሮችን ሊያካትቱ ይችላሉ። እነዚህ ጥቅማ ጥቅሞች ገንዘብ መክፈልን፣ የጠፉ ወይም የተሰረቁ ንብረቶች መመለስን፣ የጤና እንክብካቤ ወይም የስነ-ልቦና አገልግሎቶች አቅርቦትን፣ የትምህርት እና/ወይም መተዳደሪያ ድጋፍ መርሃ ግብሮች መፍጠርን፣ መደበኛ ይቅርታን እና መታሰቢያዎች ወይም ሙዚየሞች መገንባትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ የተገደቡ አይደሉም።

**የአለመደገም ዋስትና፤** ይህ የሚያመለክተው ቀደም ሲል በተፈፀሙ ጭካኔ የተሞላባቸው ድርጊቶች የተሳተፉ ወይም ጭካኔ የተሞላባቸው ድርጊቶችን ለመፍታትና ለመከላከል በቂ ያልሆኑ ሕጎችን እና ተቋማትን ለማሻሻል ነው።

**ተቋማዊ ለውጦች** የተነደፉት እንደ ፖሊስ፣ ፍርድ ቤቶች፣ የአስተዳደር ቅርንጫፎች እና የጦር ኃይል ባሉ የአገሪቱ መሠረታዊ ተቋማት ውስጥ ያሉትን የሥርዓት በደል ወይም የሙስና ቅጦችን ለመፍታት ነው። እነዚህ ለውጦች በሰብአዊ መብት ጥሰት የተከሰሱ ግለሰቦችን ማስወገድን፣ በሀገሪቱ ማእከላዊ ተቋማት ውስጥ በአጠቃላይ በህብረተሰቡ ዘንድ የመተማመን ስሜትን እንደገና ለመገንባት ማለምን እና በተቋማቱ ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች ላይ የተጠያቂነት ባህል ማሳደግን ሊያካትቱ ይችላል። እነዚህ ለውጦች የአለመደገም ቁርጠኝነትን ያሳያሉ።

**መታሰቢያ/ማስታወሻ፤** እነዚህ የማስታወስ ችሎታ የሚቀጥልባቸው ሂደቶች ናቸው። የመታሰቢያ እና የማስታወስ ውጥኖች ብዙ አይነት ቅርጾችን ሊወስዱ ይችላሉ፤ እና አብዛኛውን ጊዜ ለተጎጂዎች እውቅናን ለመስጠት እና የእርቅ እና የማህበራዊ ትስስር ማሻሻል ሰፊ ሂደት ላይ አስተዋፅኦ ለማድረግ ይፈልጋሉ።

**የመታሰቢያ/ማስታወሻ** ጥረቶች ለተጎጂዎች እውቅና የመስጠት ምሳሌያዊ መንገድን፣ ለአጠቃላይ ህዝብ እና ለወደፊት ትውልዶች ቀድመው ስላለፉ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ማስተማርን እና የሞራል ንቃተ ህሊናን ከፍ ለማድረግ እና ለወደፊቱ ጭካኔ የተሞላባቸው ድርጊቶች እንዳይደገሙ ለማድረግ የማስታወስ ችሎታን መጠበቅን ያካትታሉ። አብዛኛውን ጊዜ መታሰቢያዎች እና ሙዚየሞች ለተለያዩ ማህበረሰቦች አባላት በግጭት ልምዳቸው ዙሪያ ያሉ ልዩ ልዩ እውነቶችን እንዲገልጹ እድሎችን ይሰጣሉ።

## ለሽግግር ፍትህ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ አቀራረቦች

በሽግግር የፍትህ ማዕቀፍ ውስጥ ለአምስቱም ምሰሶዎች ሁለቱም መደበኛ እና ኢ-መደበኛ አቀራረቦች አሉ።

መደበኛ አቀራረቦች የሚመሩት በመንግስት ወይም በክልላዊ ወይም በአለም አቀፍ አካል ሲሆን አንዳንድ ጊዜ የተገለሉ ዜጎችን ተሳትፎን ወይም ማካተትን መሥዋዕት አድርገው ትላልቅ እይታ ባላቸው የሽግግር ፍትህ ስልቶች ልክ እንደ ላለፉ ጭካኔ ለተሞላባቸው ድርጊቶች በጣም ተጠያቂ የሆኑትን፣ ተጠያቂ ማድረግ ወይም ላለፉ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶች ድርጊትን በተመለከተ የታሪክ መዛግብትን ማስተካከል ላይ በማዘንበል ያተኩራሉ።

በብዙ አጋጣሚዎች ኢ-መደበኛ የአካባቢ-ደረጃ አቀራረቦች መደበኛ አቀራረቦችን ማሻሻል ወይም በመደበኛ አቀራረቦች የሚቀሩ ክፍተቶችን ማሟላት ይችላሉ፤ እና በአንዳንድ አጋጣሚዎች በአካባቢ-ደረጃ አቀራረብ ውስጥ መሳተፍ ወደ ይበልጥ መደበኛ በሆነ አቀራረብ ለመሳተፍ መሸጋገርያ ሊሆን ይችላል። ኢ-መደበኛ ወይም የአካባቢ-ደረጃ አቀራረቦች እንደ አውድ ሊለያዩ ይችላሉ፣ በአጠቃላይ ለማህበረሰብ ፍላጎቶች የበለጠ ምላሽ ይሰጣሉ እና አብዛኛውን ጊዜ እንደ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባሉ መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት ይመራሉ።

ውጤታማ የሽግግር የፍትህ ስልቶች በተለያዩ ተዋናዮች መካከል ተሳትፎ ያስፈልጋቸዋል፤ ነገር ግን መደበኛ ስልቶች፣ በመንግሥት ካልተደገፉ ወይም ካልተጀመሩ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና የሰርቫይቨር ኔትዎርኮች ጉልህ ተፅዕኖ ላላቸው ውጥኖች ፈር ቀዳጅ ሊሆኑ ይችላሉ።

| በአምስቱ የሽግግር ፍትህ ምሰሶዎች ውስጥ አንዳንድ የመደበኛ እና የኢ-መደበኛ አቀራረቦች ምሳሌዎች ከዚህ በታች ይገኛሉ፦ | |
|---|---|
| **እውነት** | • መደበኛ ስልቶች በመንግስት የተፈቀዱ የእውነት ኮሚሽኖች፣ የፍትህ ጉዳዮች፣ የእውነታ አፈላላጊ አካላት እና የሀገር አቀፍ የትምህርት ስርአተ ትምህርት። <br> • ኢ-መደበኛ የአካባቢ-ደረጃ አቀራረቦች ማህበረሰቡን መሰረት ያደረጉ ስብሰባዎች እና ውይይቶች፣ የአፈ-ታሪኮች ስነዳ፣ የማህበረሰብ ማህደሮች መፍጠር እና በተከሰቱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ላይ የማንቃት ሥራ ዘመቻዎች። |
| **ፍትህ** | • መደበኛ ስልቶች በአለም አቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት (ICC)፣ በአለም አቀፍ ፍርድ ቤቶች፣ በቅይጥ ፍርድ ቤቶች፣ በሀገር ውስጥ ክሶች እና ጉዳዮች በአለም አቀፋዊ ፅንሰ ሀሳብ ስር የቀረቡ ክሶች። <br><br> • ኢ-መደበኛ የአካባቢ-ደረጃ አቀራረቦች ባህላዊ የፍትህ ሂደቶች የተወሰኑ ጥሰቶች ለደረሰባቸው ተጎጂዎች እርማትን የመስጠት መንገድ ተብለው በረዥም ጊዜ ውስጥ በማህበረሰቦች የተነደፉ እና ተቀባይነት ያገኙ የተለመዱ ተግባራት ናቸው። |
| **ማካካሻዎች** | • መደበኛ ስልቶች መደበኛ ስልቶች ተምሳሌታዊ ሊሆኑ የሚችሉት በብሔራዊ መታሰቢያ፣ በሐውልቶች ወይም መንግስት በይፋ ይቅርታ ስጠይቅ ነው። እንዲሁም ቁሳቁሳዊ ሊሆኑ የሚችሉት በገንዘብ ማካካሻ፣ በሕክምና ዕርዳታ፣ መሰረተ ልማቶችን ለማኅበረሰቦች በማቅረብ እና በመሬት ማስመለስ ነው። <br><br> • ኢ-መደበኛ የአካባቢ-ደረጃ አቀራረቦች የስኮላርሺፕ እና የትምህርት ድጋፍን፣ የሙያ ስልጠና መርሃ ግብሮችን እና የተጎጂዎችን ቤት መልሶ መገንባትን ሊያካትቱ ይችላል። |
| **የአለመደገም ዋስትና** | • መደበኛ ስልቶች በመንግስት ማጣራትን እና ማጋለጥን፣ የፀጥታ ዘርፍ ተሃድሶን፣ ትጥቅ ማስፈታትን፣ የማቋቋሚያ እና የመልሶ ማቋቋም መርሃ ግብሮችን እና የፍርድ ስርዓት ተሃድሶን ሊያካትት ይችላል። <br><br> • ኢ-መደበኛ የአካባቢ-ደረጃ አቀራረቦች የሲቪል ማህበረሰቡን ሚና ለማጠናከር፣ የሲቪል ማህበረሰብ ተዋናዮችን ትንኮሳ ለማስቆም፣ በተለምዶ ከህግ ጥበቃ የተገለሉትን ሴቶች፣ ልጃገረዶች እና አናሳ ብሄረሰቦች ለማብቃት እና የክስተቶችን ትረካ ወይም መታሰቢያ/ማስታወሻ በባህላዊ እና ጥበባዊ መንገዶች ለማቅረብ የሚሰሩ ውጥኖች ያካትታል። |
| **መታሰቢያ/ማስታወሻ** | • መደበኛ ስልቶች ይፋዊ የመታሰቢያ ቀናት፣ ጭካኔ የተሞላባቸው ድርጊቶች የተፈፀመባቸውን ቦታዎች መጠበቅ እና የህዝብ ቦታዎችን ስም መቀየር። <br><br> • ኢ-መደበኛ የአካባቢ-ደረጃ አቀራረቦች ያልታቀዱ መታሰቢያዎች፣ የማህበረሰብ የአፈ-ታሪክ መርሃ ግብሮች፣ ለተጎጂዎች እውቅናን የሚሰጡ የግድግዳ ሥዕሎች እና የሽብልቅ ስራዎች፣ የፎቶ ኤግዚቢሽኖች እና ዘጋቢ ፊልሞች እና የማህበረሰብ መታሰቢያ የአትክልት ስፍራዎች። |

ለአስርት አመታት ከዘለቀው የሀገር ውስጥ የጦርነት ግጭት በኋላ የመጣውን መዘዝ ለመቋቋም **ኮሎምቢያ** በ2016 በመንግስት እና በኮሎምቢያ አብዮታዊ ጦር ሃይሎች፦ የህዝብ ጦር (FARC-EP) መካከል የተደረሰውን ሁሉን አቀፍ የሰላም ስምምነት[6] ተግባራዊ በማድረግ ወደ ሰላም፣ እርቅ እና ፍትህ መጠነ ሰፊ መንገድ አካሂዳለች።[7] የሰላም ሂደቱ እና ቀጣዩ ስምምነት የተጎጂዎችን የተጠያቂነት፣ የእውነት እና ማካካሻ መብቶችን ያማከሉ ነበር። ለተጎጂዎች መጠነኛ እፎይታ ቢሰጥም ትግበራው ግን ከፍተኛ እንቅፋት ገጥሞታል። ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት በግጭቱ ጊዜ ውስጥ በስፋት የተከሰቱ ሲሆን የአካባቢው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የተጎጂዎች ተሟጋቾች የስርዓታዊ ውድቀቶችን እና በሴቶች ህይወት ውስጥ ቀጣይነት ያለው የአባቶች ጭቆና ቅጥያ መሆኑን እንደሚያሳይ ጠቁመዋል።[8] ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃትን ለመፍታት በከፍታ እይታ፣ በምርመራ እና በእንቅስቃሴ አንዳንድ እድገቶች በመኖራቸው በህግ አውጭው ሂደት ውስጥ የተከናወኑ ተግባራትን እና ጥቂት ብይኖችን ያስገኙ ቢሆንም ከፍተኛ የሆነ ከቅጣት ማምለጥ አሁንም አለ፣ የመከላከያ እርምጃዎች ይጎድላሉ እናም የተጠናከረ የምርመራ እርምጃዎች እና የበለጠ ጥብቅ ቅጣቶች ያስፈልጋሉ።[9]

በ2015 **ስሪላንካ** ለተጎጂዎች እርምት ለመስጠት እውነትን፣ ፍትህን እና ተጠያቂነትን ለመከታተል ቃል ገብታለች። ይህ ለአራት የሽግግር የፍትህ ሂደቶች እቅዶችን ያጠቃልላል፦ የተሰወሩን ሰዎች የመፈለግ ስልት፣ የማካካሻ ቢሮ፣ የእውነት ኮሚሽን እና የፍርድ ስልት። እስካሁን ድረስ ከአራቱ የሽግግር የፍትህ ሂደቶች ሁለቱ ብቻ ተቋቁመዋል—የጠፉ ሰዎች ቢሮ እና የማካካሻዎች ቢሮ—እና በቂ የሆነ ድጋፍ አላገኙም።[10] ይህም መንግስት ለሽግግር ፍትህ አላማዎች ባለው ቁርጠኝነት/ቆራጥነት ላይ የዜጎችን እና የተጎጂዎችን እምነት በእጅጉ ሸርሽሯል።

ቦስኒያ እና ሄርዞጎቪና፣ ኮሶቮ፣ ሰሜን መቄዶኒያ እና ሰርቢያ—በጥቅሉ **ምዕራባዊ ባልካኖች**—በ1990ዎቹ የተካሄዱትን ጦርነቶች ውርስ እና የቀጠለውን ጥልቅ ክፍፍል ለመፍታት በተለያዩ የሽግግር ፍትህ እና የእርቅ ስራዎች ላይ ተሰማርተዋል። ስለቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ በዓለም አቀፍ የወንጀል ፍርድ ቤት ከተካሄዱት ከፍተኛ እውቅና ካላቸው የፍርድ ሂደቶች ባሻገር በተለይ በማህበረሰብ ደረጃ እርቅን በማስፈን ረገድ ትልቅ ስኬት የተገኘው እውነትን በመናገር፣ በጥበብና በባህል፣ በመታሰቢያነት፣ በውይይት እና በትምህርት ነው።[11] እነዚህ ጥረቶች የሲቪል ማህበረሰብ በኢ-መደበኛ አቀራረቦች መደበኛ የሽግግር ፍትህ ሂደትን በማሟላት፣ በማጠናከር እና/ወይም ተደራሽነቱን በማስፋት ረገድ ሊጫወቱት የሚችለውን ሚና ያሳያሉ።

በ2017 አምባገነኑ ያህያ ጃሜህ **ጋምቢያን ሲለቁ** ሀገሪቱ የሽግግር ፍትህ ሂደት ጀመረች። አዲስ የተመረጠው መንግሥት የጸጥታ ሴክተር ማሻሻያ ስልትን፣ የቀድሞ አምባገነኑን የፋይናንስ ጉዳዮች አጣሪ ኮሚሽን፣ የሕገ መንግሥት ገምጋሚ ኮሚሽን እና የእውነት፣ የእርቅና የማካካሻዎች ኮሚሽን አቋቋመ። መሻሻል ቢኖርም እንደ ሴት ተሳታፊዎች ደህንነት ያሉ በርካታ ጉልህ ጉዳዮች ሂደቶቹን ተፈታትነውታል።

**ኬንያ** ከምርጫ በኋላ ከ2007-2008 ከፍተኛ የሆነ ወሲባዊ ጥቃትን ጨምሮ ሌሎች ወንጀሎችን አጋጥሟታል። በርካታ የሽግግር ፍትህ ጥረቶች ለጥቃቶቹ የተወሰነ ተጠያቂነት እንደሚሰጡ ቃል ገብተው ነበር። እነዚህ ጥረቶች የእውነት እና እርቅ ኮሚሽን (2008–2013)፣ የICC ሂደቶች (2010–2015)፣ የፕሬዚዳንት ኬንያታ ይፋዊ ይቅርታ እና ማካካሻዎችን ለመስጠት የተሃድሶ ፍትህ ፈንድ (2015) የገቡትን ቃል ያካትታሉ። ነገር ግን የእውነት እና የእርቅ ኮሚሽን ውጤቶች እና በርካታ ምክረ ሃሳቦች በፓርላማ ተስተጓጉለዋል፣ ICC በስድስት ወንጀል ፈፃሚዎች ላይ የመሰረቱት ክሶች ምስክሮችን ማስፈራራት አለ በተባለበት ሁኔታ በሙሉ ተሰርዟል ወይም አልተረጋገጡም፣ ማካካሻዎችን ለመስጠት የተገባው ቃል እውን ሊሆን አልቻለም እና የብሄራዊ ፍርድ ቤቶች አብዛኛውን ጊዜ ከምርጫ በኋላ የተፈጸሙ ወንጀሎችን ለመፍታት አልቻሉም። ከምርጫው በኋላ በተከሰቱት ሁከትና ብጥብጥ ሰርቫይቨር ሴቶች እስካሁን እየደረሰባቸው ያለውን የስሜት ቀውስ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር በመገንዘብ የሲቪል ማኅበራት አንድ ላይ በመሰብሰብ ቡድን መስርተው ሴቶቹን ለመደገፍ የሚያስችል መንገድ ፈልገው ነበር። ቡድኑ ለወሲባዊ ወንጀሎች የግለሰብን ተጠያቂነት ከመጠየቅ ይልቅ የኬንያ መንግስትን ሰብአዊ መብቶችን የማስከበር ግዴታውን ባለመወጣቱ ፍርድ ቤት አቀረበ። በ2013 ስድስት ሴቶች እና ሁለት ወንዶች የኬንያ መንግስት ችላ በማለቱ መንግስቱ ላይ ክስ መሰረቱ። በ2020 የኬንያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ገዢን ጥፋተኛ ብሎታል። ሃኪሞች ለሰብአዊ መብቶች በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ መሰረት የፍርድ ቤቱ ግኝት መንግስት “ከምርጫ በኋላ ብጥብጥ በነበረበት ጊዜ SGBV [በወሲብ እና ሥርዓተ-ጾታ ላይ የተመሰረተ ጥቃት ጋር የተያያዘ ወንጀሎችን] ነፃ እና ውጤታማ የሆኑ ምርመራዎችን ማድረግ እና ክስ መመስረት አልቻለም”[12] የሚል ነው። ይህ ጠቃሚ ውሳኔ ሌሎች ሰርቫይቨሮች አሁን በፍትህ ሂደት ለነዚህ ላለፉ ወንጀሎች ፍትህ ፍለጋቸውን እንዲቀጥሉ ሊበረታቱ እንደሚችሉ ተስፋ ሰጪ ምሳሌ ነው። እንዲሁም የወሲባዊ ወንጀሎች ላይ ትክክለኛ ምርመራ ለማድረግ ለውጦች እንደሚያስፈልጉ ለፖሊስ መልእክት ይሰጣል።

## 5. የሚጠቆሙ ለውጦች

GIJTR ከእውነት፣ ከፍትህ እና ከፈውስ አንፃር ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት አብዛኛው አወንታዊ ለውጥ የሚመጣው በሰርቫይቨሮች እና በዙሪያቸው ባሉ ማህበረሰቦች ቀጣይነት ያለው ጥረት መሆኑን ተመልክቷል። ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ወንጀሎችን በብቃት ለመፍታት እና በሽግግር ፍትህ ሂደቶች ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት የአካባቢያዊ ባለቤትነት ያለውን ጠቀሜታ በመገንዘብ ካለፉ የሽግግር ፍትህ ሂደቶች የተወሰዱ የለውጥ ዘርዘሮች ከዚህ በታች አሉ። የነዚህም ዓላማ የሽግግር ፍትህ ሂደቶች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮች በእውነት ተደራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ፣ የሰርቫይቨሮቹን ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት እና ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት መሰረታዊ መንስኤዎችን ኢላማ ማድረግ ነው። እነዚህ የለውጥ ሃሳቦች ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ጋር በተገናኘ ካለፉ የሽግግር ፍትህ ሂደቶች የተወሰዱ የትምህርቶች ስብስብ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ እና ያሉትን የመንግስት ማዕቀፎች በመገምገም እና በሽግግር ፍትህ ሂደቶች ወይም በብሄራዊ ህግ አውጭ አካላት ውስጥ ልዩ ለውጦችን አጥብቆ በመደገፍ ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት ሰርቫይቨሮችን በተሻለ ሁኔታ ለመደገፍ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡-[13]

- የሕግ አውጭው ማዕቀፉ ምንም ዓይነት አድሎአዊ ድንጋጌዎች ሳይኖር በቂ የሥርዓተ-ጾታ ጥበቃ ማድረጉን እና በተለይም ግብረ ሰዶማዊነት እና የተመሳሳይ ጾታ ድርጊቶች ወንጀል አለመሆናቸውን ማረጋገጥ።
- SGBV ሰርቫይቨሮችን ፍትህ እንዲያገኙ እና ከሕግ ተጠያቂነት የማምለጥ ችግርን ለማስወገድ የሚደረገውን ጥረት መጠናከሩን ማረጋገጥ።
- ሁሉም የማካካሻ መርሃ ግብሮች ተጎጂዎችን ያማከሉ እና ሥርዓተ-ጾታን የሚያገናዝቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ።

- የማስታረቅ መርሃ ግብሮች ከእቅድ ጀምሮ እስከ ትግበራ ደረጃዎች ድረስ በማህበረሰብ ከተመሩ ሰፊ ምክክር የተገኙ መሆናቸውን ማረጋገጥ።
- በግንባር ቀደምትነት በወሲብ እና ሥርዓተ-ጾታ ላይ የተመሰረተ የጥቃት ግንዛቤን ለማሳደግ ያለሙ መርሃ ግብሮችን ማጠናከር።
- ሴቶችን ለማብቃት እና የሥርዓተ-ጾታ ፍትሃዊነትን እና በመንግስት እና በግል ሴክተሮች ውስጥ እኩል ውክልናን ለመደገፍ እርምጃዎችን መውሰድ።
- የወሲባዊ እና የስነ-ተዋልዶ ጤና እና መብቶች ግንዛቤን ለማሳደግ አጠቃላይ የሥርዓተ-ጾታ፣ የወሲባዊ እና የስነ-ተዋልዶ ጤና ትምህርትን በትምህርት ቤቶች ማስተዋወቅ።
- ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ ቡድኖችን ፍላጎት የሚያሟሉ በቂ የወሲባዊ እና የስነ-ተዋልዶ ጤና አጠባበቅ አገልግሎቶች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ጥረቶችን ማጠናከር።
- እንደ LGBTQIA+ ያሉ ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ ማህበራዊ ቡድኖችን እና ማህበረሰቦችን ለመደገፍ እና ለመጠበቅ ጥረቶችን ማጠናከር።

### የመጨረሻ ማስታወሻዎች


1 "'ከግጭት ጋር የተያያዘ ወሲባዊ ጥቃት' የሚለው ቃል አስገድዶ መድፈርን፣ ወሲባዊ ባርነትን፣ የግዳጅ ሴተኛ አዳሪነትን፣ የግዳጅ እርግዝናን፣ የግዳጅ ጽንስ ማቋረጥን ውርጃን፣ አስገዳጅ ስቴራላዜሽን፣ የግዳጅ ጋብቻን እና ሌላ ወሲባዊ ጥቃቶችን እና ሌሎች ሊወዳደሩ የሚችሉ ክብደት ያላቸውን ጥሰቶችን በሴቶች፣ በወንዶች፣ በሴት ልጆች ወይም ወንዶች ልጆች ላይ የሚደርስ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከግጭት ጋር የሚገናኝ ማንኛውንም ዓይነት ወሲባዊ ጥቃት ያመለክታል። ይህ ግንኙነት አሸባሪዎችን ጨምሮ መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ የታጠቁ ቡድኖች ጋር የተገናኙ የድርጊት ፈፃሚዎች መገለጫ ግልጽ ሊሆን ይችላል፤ በተደጋጋሚ የፖለቲካ፣ የብሄር ወይም የሃይማኖት አናሳ ቡድን አባል የሆኑ ወይም ናቸው ተብለው የሚገመቱ የተጎጂዎች መገለጫ፤ በሆነ ወይም ነው ተብሎ በሚገመቱ የወሲባዊ ዝንባሌ ወይም የፆታ ማንነት ላይ ያነጣጠረ፤ ከጠቃላይ የመንግስት ውድቀት፣እንደ መፈናቀል እና ህገወጥ የሰው ዝወውር እና/ወይም የተኩስ አቁም ስምምነት ጥሰት የመሳሰሉ ድንበር ተሻጋሪ መዘዞች ጋር የሚያያዝ ተጠያቂነት አለመኖር ሁኔ። ቃሉ ለወሲባዊ ጥቃት ውይም ብዝበዛ በግጭት ሁኔታዎች ውስጥ የሚፈም የሰዎች ህገውጥ ዝውውርን ያጠቃልላል።" Conflict-Related Sexual Violence Report of the United Nations Secretary-General (S/2019/280).

2 . Johnson K, Asher J, Rosborough S, et al., "Association of Combatant Status and Sexual Violence With Health and Mental Health Outcomes in Postconflict Liberia," JAMA 2008;300(6):676–690 (2008), https://jamanetwork.com/journals/jama/fullarticle/182379.

3 Kiss, L., Quinlan-Davidson, M., Pasquero, L., et al., "Male and LGBT survivors of sexual violence in conflict situations: a realist review of health interventions in low-and middle-income countries," Conflict and Health 14, 11 (2020), https://doi.org/10.1186/s13031-020-0254-5.

4 UN General Assembly, "Basic Principles and Guidelines on the Right to a Remedy and Reparation for Victims of Gross Violations of International Human Rights Law and Serious Violations of International Humanitarian Law," resolution adopted by the General Assembly, 21 መጋቢት 2006 , A/RES/60/147, https://www.refworld.org/docid/4721cb942.html.

5 Remarks of the UN's Special Representative of the Secretary-General on Sexual Violence in Conflict: https://www.un.org/sexualviolenceinconflict/statement/remarks-of-srsg-patten-at-unga76-side-event-preventing-addressing-conflict-related sexual violence-as-a-tool-of-war-co-hosted-by-the-office-for-global-womens-issues-us-department-of-state-search-f/

6 Peace Agreements Database, "Final Agreement to End the Armed Conflict and Build a Stable and Lasting Peace," https://www.peaceagreements.org/wview/1845/Final%20Agreement%20to%20End%20the%20Armed%20Conflict%20and%20Build%20a%20Stable%20and%20Lasting%20Peace.

7 The Council on Foreign Relations, "Colombia's Civil Conflict," https://www.cfr.org/backgrounder/colombias-civil-conflict.

8 Esther Marina Gallego Zapata, Ruta Pacífica de las Mujeres "Colombia Case Study," [NEED DATE, OFFICIAL TITLE AND URL].

9 Ibid.

10 OHCHR, "Sri Lanka: Experts dismayed by regressive steps, call for renewed UN scrutiny and efforts to ensure accountability," https://www.ohchr.org/en/press-releases/2021/02/sri-lanka-experts-dismayed-regressive-steps-call-renewed-un-scrutiny-and.

11 Huma Haider, "Transitional justice and reconciliation in the Western Balkans: Approaches, impacts and challenges," ጥር 25, 2021, https://opendocs.ids.ac.uk/opendocs/handle/20.500.12413/16471.

12 Physicians for Human Rights, "Kenya Submission to the United Nations Special Rapporteur on Violence against Women, its Causes and Consequences Ms. Dubravka Šimonovič," 31 ታህሳስ 2020, https://www.ohchr.org/Documents/Issues/Women/SR/RapeReport/CSOs/166-kenya.pdf.

13 These reform suggestions are drawn from the Women in Liberation and Leadership's "WILL TRRC Shadow Report on SGBV," https://www.womeninliberation.org/reports.